# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 46 መጋቢት 24 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

‹‹መለስ ዜናዊ እና በመንግስቱ ውስጥ ያሉ እንዳንዶች በኢትዮጵያና በጎረቤት ሶማሊያ ለፈጸሟቸው ሰፊ የመብት ረገጣዎች እና ወንጀሎች እነሱም ሊጠየቁ እንደሚችሉ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ .....››

ዶ/ር ግሬጎሪ ስታንተን **የጀኖሳየድ ዋች ፕሬዚዳንት**

## ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ወደ ዝዋይ እንደሚዛውሩ ተገለጸ

የአንድነት ለዴሞክራሲና ፍትህ ሊቀመንበር የሆኑት ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ከቃሊት ወህኒ ቤት ወደ ዝዋይ እንደሚዛውሩ ተነግሯቸዋል። የግንቦት ሰባት ሪፖርተር የቃሊቲ ወህኒ ቤት ፖሊሶችን አነጋግሮ እንደዘገበው የወህኒ ቤቱ ይህን ማስጠንቀቂያ ሊሰጥ የቻለበት ምክንያት ጠበቃቸው አቶ ተስፋዬ ደረሰ ወ/ሪት ብርቱካን ከታሰሩበት ጊዜ አንስቶ ብቻቸውን በአንድ ጨለማ ቤት ውስጥ ታስረው የሚገኙ እንደሆኑና በወዳጅ ዘመዶቻቸው የመጎብኘት ሰብአዊ መብታቸውን ተገፈው እየተሰቃዩ መሆናቸውን በመግለጽ መጋቢት ዘጠኝ ቀን በፌዴራል መደበኛ ፍርድ ቤት ዘጠነኛ ፍትሃ-ብሔር ችሎት ከመሰረቱት ክስ ጋር የተገናኘ እንደሆነ ገልጸዋል።

እንደ ፖሊሶቹ ከሆነ የማረሚያ ቤቱ ሃላፊዎች የሆኑት አብርሃም ወልዳረጋይ፣ አበበ ዘሚካኤልና የማነህ ተክሉ ሆነው የወ/ረት ጠበቃ ክስ ከመሰረተ በኋላ በነጋታው ክሱን ለማስተባበል ምን ዘዴ እንቀይስ ብለው ሲወያዩ መስማታቸውን ገልጸዋል። በተለይ ስሙ እንዳይጠቀስ የጠየቀ አንድ ፖሊስ ከክሱ መመስረት በኋላ የተወሰዱትን እርምጃዎች እንዲህ ሲል ገልጿል። ክሱ ከተመሰረተ በኋላ የማረሚያ ቤቱ ሃላፊዎች የሆኑት አብርሃም ወልዳረጋይ፣ አበበ ዘሚካኤል እና የማነህ ተክሉ ስብሰባ አድርገው በወህኒ ቤቱ እስረኞችን እንዲሰልሉ ከሚያስቀምጧቸው ሴት እስረኞች መካከል የተመረጡ ሴት እስረኞች በተለያዩ ቀናት ሌሊት ወ/ሪት ብርቱካን ወደታሰሩበት ክፍል እየተወሰዱ እንዲያድሩ ማድረግ መጀመራቸውንና እነዚህም ሰላይ እስረኞች ተሳደቡ ተብሎ ትዕዛዝ እንደሚሰጣቸውም በምሬት ይናገራል። እስረኞቹን እያመጡ ማሳደር ለምን እንዳስፈለገም ሲገልጽ ክሱ የተመሰረተበት ፍርድ ቤት ለማስመሰልም ቢሆን ስለወ/ሪት ብርቱካን አያያዝ ወህኒ ቤቱ ምላሽ እንዲሰጥ ያዘዘ በመሆኑና ምናልባት ዳኛው በስህተት ወ/ሪት ብርቱካን እንዲቀርቡ ቢያዝና ፍርድ ቤት ቢመጡ ብቻቸውን ታስረው እንደነበር መግለጽና የደረሰባቸውን ግፍ መናገር እንዳይችሉ ለማድረግ የተዘየደ ዘዴ እንደሆነ ይገልጻሉ።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን የኤፈርት ምክትል ሃላፊ ሆኗ ተሾመች

የፋሽስቱ የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን የኤፈርት ምክትል ሃላፊ ሆኗ መሾሟ ተገለፀ:: ይህ ሹመት የሚናገረው ነገር ቢኖር፥ ሰዎቹ ይቅር ለሌላው ኢትዮጵያዊ፣ በደሙና በአጥንቱ ክስካሽ ለድል ያበቃቸውን እና ላለፉት 18 ዓመታት ዘብ ቆሞ ለሚጠብቃቸው ታጋይ የትግራይ ተወላጅ የመጨረሻ ንቀት ማሳያ ነው ሲሉ ታዛቢዎች አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል።

ወያኔ ከተሰነጠቀ በሓላ በሹመት ላይ ሹመት እየተደረበላት እዚህ የደረሰቸው አዜብ መስፍን ገንዘብ እንደልብ ካለጠያቂ በሚዛቅበት ኤፈርት መሾሟ እንኳን ዘንቦብሽ ድሮም ጤዛ ነሽን ያስታውሳል ተብሎአል። በድህ ስም ተለምኖ የመጣን ገንዘብ ካለምንም ሀፍረት እንደምትዘርፍ የታወቀላት አዜብ ከጥቂት ወራት በፊት ቴሌኮሚኒኬሽንን አስገድዳ ህንፃዋን በ60 ሚሊዮን ብር ለአስር አመት እንዲከራይ ማድረጓን መዘገባችን የሚታወስ ነው።

አዜብ መስፍን በምርጫ 97 ወልቃይትን ወክላ አሸነፈች ተብላ ፓርላማ መግባቷ ሳያንስ የፓርላማው የማህበራዊ ጉዳዮች ሀላፊ እንደሆነች ይታወቃል። የማትገባበት ኮሚቴ የሌላት አዜብ የወያኔ ማእከላዊ ኮሚቴ አባል እና የሌሎች በርካታ ኮሚቴዎች ሀላፊ እንደሆነች ይታወቃል። አዜብ አደባባይ መዋል ከመጀመርዋ በፊት በኤፍርት ስር የሚተዳደረው ሜጋ ማተሚያ ቤት ስራ አስኪያጅ እንደነበረችም የሚታወቅ ነው።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጀኖሳይድ ዋች መለስ የፈፀመው የዘር ማጥፋ ወንጀል የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር እንዲመረምር ጠየቀ።

የድርጅቱ ፕሬዚደንት ዶ/ር ግሬጎሪ ስታንተን ለኮሚሺነሩ በፃፉት ደብዳቤ ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት በቅርቡ በሱዳኑ መሪ ላይ የእስር መጥሪያ ሲሰጥ፣ ቀድመው ከተቃወሙት መሃከል መለስ ዜናዊ አንዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት መለስ ዜናዊ እና በመንግስቱ ውስጥ ያሉ እንዳንዶች በኢትዮጵያና በጎረቤት ሶማሊያ ለፈጸሟቸው ሰፊ የመብት ረገጣዎች እና ወንጀሎች እነሱም ሊጠየቁ እንደሚችሉ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው ብለዋል።

ፕሬዚደንቱ በደብዳቤያቸው፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ስር የሰደደና በመንግስት የተደገፈ ማን አለብኝነት፥ ወንጀል የፈጸሙ ባለስልጣናትን ከተጠያቂነት እያተረፈ ስለሆነ፣ በተባበሩት መንግስታት የሚካሄድ ገለልተኛ ማጣሪያ እጅግ አስፈላጊ ነው ብለዋል። ጨምረውም፥ “ሽብርተኝነትን እዋጋለሁ እያለ የገዛ ህዝቡን በሚያሸብረው መንግስት ከሚካሄደው ጨካኝ አፈና እና ስልት የኢትዮጵያ ህዝብ እረፍትንና ቅን የሆነን ፍትህ ሲጠባበቅ ለረዥም ጊዜ ቆይቷል ብለን እናምናለን፤” ሲሉ ኮሚሽነሩ ባስቸኳይ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄዱ ያሉት የመብት ጥሰቶች በሰፊው መመዝገባቸውን እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ገለልተኛ የማጣራት ስራ መስራታቸውን ገልጸዋል። ጀኖሳይድ ዋች፥ በጋምቤላ የተፈጸመው ግድያ የዘር ማጥፋት እና በሰው ልጆች ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው ብሎ እንደሚያምን እና፤ ሂውማን ራይትስ ዋች የተባለው ታዋቂ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋችም ሁለት ጊዜ ምርመራዎች አድርጎ የጋምቤላው ግድያ በሰው ልጆች ላይ የተፈጸመ ወንጀል የሚባለውን ወንጀል መስፈርት እንደሚያሟላ መግለጹን ጠቅሰዋል።

የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር ለሚያደርገው ማጣራት ድርጅታቸው አስፈላጊውን እርዳታ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነ የገለጹት ዶ/ር ግሬጎሪ፥ “እኛ በጀኖሳይድ ዋች ውስጥ እና በሌሎችም የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ውስጥ ያለን በተልእኳችን መሰረት፣ ወንጀሉ ከተሰራ ቢቆይ እንኳ፣ ፍትህን ለማስፈን ቆርጠን የተነሳን ነን፤” ብለዋል።

# ምርጫ ስንል፤ ምርጫ ሲሉ፤ ምርጫ 2002 በኢትዮጵያ

ወደ ፊት በሃገራችን የሚደረግ ምርጫ ምን ለማምጣት የሚደረግ ምርጫ መሆን ይገባዋል? ይህስ ምርጫ እንዴት መካሄድ ይችላል ለሚሉ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ግንቦት 7 ማንንም ግራ የማያጋባ ምላሽ ሰጥቷዋል። አንደኛ የሚቀጥለው ምርጫ በሃገራችን ለመጀመሪያ ግዜ ነጻና ፍትሃዊ የሆነ፣ ህዝብ ሰለማዊ በሆነ ሂደት፣ በምርጫው የመንግስት ስልጣን በማን መያዝ እንዳለበት የሚወስንበት ምርጫ ሊሆን ይገባዋል ብለናል። ይህ ምርጫ መለስ ዜናዊን የሃገራችን የመጨረሻው አምባገነን መሪ፣ የሚመራውንም የወያኔ ድርጅት የመጨረሻው የምርጥ ገዢ ቡድን ለማድርግ አልሞ የተነሳ ሊሆን ይገባዋል ብለናል። ሁለተኛ፣ ይህ ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሆን በስልጣን ላይ ያለውን ገዥ ፓርቲ ሆነ ሁሉንም የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ያለምንም አድልዎ በእኩልነት ማስተናገድ የሚችሉ፣ ህዝብ በነጻነት ለምርጫ መመዝገብና ድምጽ መስጠት፣ የሰጠውን ድምጽ በአግባቡ የሚቆጥሩና ከተቆጠረው ድምጽ አብላጫውን ላገኘው ስልጣን ማስረከብ የሚችሉ ገለልተኛ ተቋማት ሊኖሩ ይገባል ብለናል።

እኛ ምርጫ ስንል ይህን ማለታችን ነው። መለስ ዜናዊ ምርጫ ሲል ግን ከእዚህ የተለየ ነው። መለስ ዜናዊ ምርጫ ሲል ከምርጫ 97 በኋላ ህገወጥ በሆነ መንገድ የያዘውን ስልጣን በይስሙላ ምርጫ ህጋዊ ማድርግ ማለት ነው:: ህዝብን አፍኖ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጅና እግራቸውን አስሮ፣ መለስ ዜናዊን ራሱ ባቆመው ምርጫ ቦርድ፣ በምንደኛነት በሚያሽከረክሯቸው ዳኛዎቹና የጦር አበጋዞቹ ታጅቦ ያሻውን ያለምንም ከልካይ የሚፈጽምበትን ሂደት ነው መለስ ዜናዊና ባልደረባዎቹ ምርጫ የሚሉት:: ህዝብ በነጻነት የሚወስነው ሳይሆን መለስ ዜናዊ አስቀድሞ የወሰነውን ተግባራዊ የሚያደርግበት ሂደት ነው ለመለስ ዜናዊ ምርጫ ማለት። ስለእዚህም ነው መለስ ዜናዊ ለሚቀጥለው ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ መሆን ዋስትና የሚሰጡትን ነጻ የመገናኛ ብዙሃን፣ ገለልተኛ የፍትህ ስርአትንና ለህዝብና ለህገ መንግስት ተገዢ የሆነን የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል ጉዳይ አታንሱብኝ የሚለው:: የሚያነሱበትንም በሃገር ክህደት አንስቶ እስከ ዘር ማጥፋት ወንጀል ከሶ ለማሰር፤ ለመግደልና ለማሳደድ የማይመለሰው። መለስ ዜናዊ እያለ ያለው «እኔው የጨዋታውን ህግ አወጣለሁ፤ የመሃል ዳኛውንና የመስመር ዳኛውን እስይማለሁ፣ አስቀድሜ በጨዋታው ሰንት ጎል እንደማገባና አሸናፊ ሆኘ እንደምወጣ እነግራችኋለሁ የናንተ ስራ በጨዋታው ውስጥ ገብታችሁ እኔን በማጀብ ድሌን ማድመቅ» ነው:: በተግባር ይህ ምን እንደሚመስል ከምርጫ 97 በፊት የነበሩትን ‹ምርጫዎች› ወይንም ከምርጫ 97 ትምህርት ከቀሰምን በሁዋላ ያካሄድነውንና 99 ከመቶ ያሸነፍንበትን ‹ምርጫ› ተመልከቱ ነው የሚለን::

ምርጫ 97ን ላየና የነፃነትን ምንነት ለሚያውቅ ሕዝብ በዚህ አይነት ቀልድ ውስጥ ተሳተፍ ማለት በእውነቱ አስቀያሚ ስድብ ነው:: ግንቦት7 እንዲህ አይነቱ ነገር እንኳን ሊሞከር ሊታሰብ አይገባውም ብሏል::

በነፃና ትክክለኛ ምርጫ ወያኔ/ኢሕአዴግ ምንም እድል እንደሌለው ያውቃል:: እነመለስ ከስልጣን መውረድን ደግሞ እንኩዋን ሊቀበሉት ሊገምቱት አይችሉም:: እስከአሁን የሰሩት ወንጀል እንቅልፍ ይነሳቸዋል:: ስለዚህ በምንም አይነት ነፃ ምርጫ አያደርጉም:: ግንቦት 7 የእዚህን ቀመር ትክክለኛነት አጥብቆ ስለሚያምንበት መለስ ዜናዊና በዘረኛነት፣ በአምባገነንነትና በዘረፋ የገነኑና የገነነ ጓደኞቹ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት በሃገራችን ለመገንባት የምናደርገው ጥረት ተባባሪ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ምንም አይነት ቅዠት የለውም። መፍትሄው እነዚህን የዴሞክራሲ የእኩልነትና የአንድነት ደንቃራዎች ጠርጎ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሃገሪቱን ህዝብ በእኩልነት ማስተናገድ የሚችሉ ተቋማት ከሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶችና ከሁሉም የሃገሪቱ ዜጋ ጋር በጋራ በመምከር የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደቱን በጋራ መጀመር ነው ብለናል:: ለእዚህም የትኛውንም የትግልና የፖለቲካ ስልት፤ አመጽንም ጨምሮ በስራ ላይ ለማዋል፣ ለዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር በአመጽም ይሁን በሰላማዊ መንገድ ከሚታገሉ ሃይሎች ጋር ሁኔታው በፈቀደ መጠን ተባብሮ ለመታገል መቁረጣችንን ግልጽ አድርገናል::

የግንቦት 7 ንቅናቄ ይህንን እምነቱን ይዞ በቀጥታ መነጋገርና መተባበር ከሚችላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ተነጋግሯል:: ከእነዚህ ሃይሎች ጋር ባደረገው ወይይት የሃገራችን የፖለቲካ ድርጀቶች ስለምርጫ፣ ስለስልጣን፣ ሰለፓርቲዎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳራዊ፣ የወጭ ጉዳይና ሌሎች ፖሊሲዎች አንስተው ከመነጋገራቸው ቢፊት ቅድሚያ ሰጥተው በጋራ ሊታገሉለት፣ ሁሉንም በጋራ ሊያሰባስብ የሚችል ጉዳይ በሃገራችን ህዘብን በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አማካይነት የስልጣን ባለቤት ለማድረግ በሚያስችሉ የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታና ሂደት ላይ ብቻ ሊሆን እንደሚገባው መሰራታዊ መግባባት ላይ ደርሷል::

የግንቦት 7 ንቅናቄ ከእዚህም አልፎ በቀጥታ ሊያገኛቸው የማይችላቸውን ነገር ግን በትግል ስልታቸው «ህግንና ሰላማዊነትን ጠብቀን እንታገላለን» የሚሉ የሃገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች አቅማቸውን በጋራ በማስተባበር በሚያገኙት ጉልበት እነሱም እንደ ግንቦት 7ና ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የሚቀጥለውን ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም ይዘው ቢወጡና ይህንንም ለህዝብ አሳውቀው ህዝብን ለትግል እንዲያነሳሱ ጥሪ ሲያደርግ ቆይቷል:: ከጥቂት ወራት በፊት ንቅናቄያችን «መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ» (መድረክ) የተባለውን ቡድን መፈጠርና የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የመድረክ አባል ለመሆን የወሰነውን ውሳኔ ደግፈን ኦፊሴላዊ አቋም የወሰድነው በመድረክ ውስጥ የሚሰባሰቡ ሃይሎች የሚቀጥለውን የ2002 ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ ለማድረግ በጋራ ለመታገል ከማሰብ የላቀ ሌላ አጀንዳ አይኖራቸውም ከሚል እምነት በመነሳት ነው::

ሆኖም ግን የመጪውን የ2002 ምርጫ መቃረብ ስንመለከትና፤ እስከአሁን በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሃይሎች ይህን ምርጫ ነጻና ፍትሃዊ ለማድርግ በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርገው የጋራ አቋም ወስደው ወደ ህዝብ አለመቅረባቸውን ስንረዳ ነገሩ አሳሳቢ እየሆነብን እንደመጣ ግንቦት7 ግልጽ ማድረግ ይወዳል:: መለስ ዜናዊ ፈላጭ ቆራጭ በሆነበት ሌላ ምርጫ እንሳተፋለን አንሳተፍም? እውነተኛ ምርጫ በሃገራችን እውን እንዲሆን ምን ነገሮች መሟላት አለባቸው? እነዚህን ነገሮች ለማሟላት በጋራ ምን እናድርግ? በሃገርና ከሃገር ውጭ ለሚገኘው ህዝብ በጋራ ምን አይነት የትግል ጥሪ እናቅርብ? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተው በጋራ ሳይመከርባቸው ምርጫው እየተቃረበ መምጣቱ ነው ግንቦት7ን የሚያሳስበው:: ጭንቀታችን በጋራ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ሃይሎች አስቀድመው በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መክረው የጋራ አቋም ይዘው በግዜ ወደ ህዝብ ካልወረዱ እያንዳንዳቸው የመለስ ዜናዊ የጥቃት ሰለባ መሆናቸው አይቀርም የሚል ነው:: ይህ ስጋታችን እውን ከሆነ ድርጅቶች የተዘበራረቀ አቋዋም ይወስዳሉ:: ጫናው እየገፋ ሲሄድ የተወሰኑት እጃቸውን ይሰጣሉ፤ እጅ አንሰጥም ያሉት ለብቻቸው ይመታሉ የእዚህም ውጤት ደግሞ የመለስ ዜናዊን የክህደትና የግፍ እጅ ማጠናከር፣ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መዳከም፣ የህዝብ ቅስም መሰበር ይሆናል:: ይህንን እያወቁ መድገም ደግሞ እጅግ አሳፋሪ ነው የሚሆነው:: "እንቅፋት አንዴ ቢመታህ ጥፋቱ የድንጋዩ ነው፤ ሁለተኛ ከመታህ ግን ድንጋዩ አንተ ነህ፤ ነው የሚሉት አበው?"

የግንቦት7 ንቅናቄ ይህን መልእክት ሲያስተላልፍ የትኛዎቹም ድርጅቶች የራሳቸው ነጻነት እንዳላቸውና ስራቸውን በፈለጉትና በመረጡት መንገድ የመስራት መብት እንዳላቸው አጥቶት አይደለም:: ድፍረታችን፣ የዴሞክራሲን ጥያቄ በሚመለከት ግንቦት 7 ከእነዚህ በኢትዮጵያችን የዴሞክራሲ መብቶች ባለመከበራቸው መከራቸውን ከሚያዩት የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ከጋራ ስቃይ የሚመነጭ የመንፈስ ወዳጅነትና አጋርነት አለኝ ብሎ ከማሰብ ወገናዊ ተቆርቋሪነት የመነጨ ነው:: የሁላችንም ፍላጎት ቅድሚያ የሚሰጠው የምርጦችን አገዛዝ፣ ህዝብ በነጻነት በተሳተፈበት፣ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ በሚሰየም አስተዳደር መተካት ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል:: በመሆኑም ይህንን ሂደት ያበረታታል ወይም ይጎዳል በሚሉ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ ከይሉኝታ ባሻገር መወያየት ጉዳዩን የድርጅቶች የውስጥ ጉዳይ ሳይሆን የአገርና የጋራ ፖለቲካ ጉዳይ መሆኑን ማስረገጥ ነው ብለን አጥብቀን እናምናለን:: በእነዚህ አስተያየቶች አማካይነት ልዩነቶቻችንን አስወግደን፣ እንደብረት የጠነከረ የጋራ አቋም እስከወሰድን ድርስ ከመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ መንጋጋ ነጻነትንና ዴሞክራሲን በቀላሉ መንጭቅን ማውጣት አያቅተንም:: ይህ የጋራ አመለካከት ምን መሆን እንደሚገባው ግንቦት7 የራሱን ወርውሯል:: ሌሎችም ድርጅቶች በእዚህ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ አቋማቸውን ግልጽ አድርገው በጋራ መርህ ላይ ለቆመ የፖለቲካ መተባበር፤ ተባብሮም ከሕዝብ ጋር ሆኖ መታገል፤ ታግሎም ይህን ቆሻሻ ስርአት ለመጣል የምንሰራበት ሊሆን ይገባዋል::

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።**

g7radio@ginbot7.org

# ሃይለ ሀሳብ

## ተደበቆ የማለ በአደባባይ ይክዳል
## ከዝግጅት ክፍላችን

የዛሬ ሁለት አመት መለስ ዜናዊ ይህ በጉልበት የያዘዉ የሥልጣን ዘመኑ ሲያበቃ የጠቅላይ ሚኒስተርነቱን ቦታ እንደሚለቅ ተናግሮ ነበር፤ ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ስሙን እንኳን ላያነሳ አንቅሮ እንደተፋዉ በዉል የተረዳዉ ከሀዲዉ መለስ የዛሬ ሁለት አመት ሳይታመም የተናዘዘዉን የሐሰት ኑዛዜ ማንም እንዳልሰማለት ስለተረዳ “የሞኝ ዘፈን ሁል ጊዜ አበብዬ” እንዲሉ ያንኑ ከሁለት አመት በፊት ያሰማንን የስልጣን በቃኝ ዘፈኑን ዛሬም በድጋሚ እያሰማን ነዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ መለስ ዜናዊ እንዴት ሥልጣን ላይ እንደወጣና እንዴት ሥልጣን ይዞ መቆየት እንደቻለ በሚገባ ያዉቃል፤ ስለሆነም መለስ ሥልጣን በቃኝ ወይም አልበቃኝም ቢል ያ የራሱ ጉዳይ ነዉ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የወያኔ ዘመንና የመለስ ዜናዊ ባዶ ተስፋ በቅቶታል።

መለስ ዜናዊ አልገባዉ አለ እንጂ የሚገባዉ ቢሆን ኖሮ የፖለቲካ ሥልጣን በተለይ አገር መሪነት እሱ በፈለገዉ ጊዜ ሁሉ አብሮት የሚኖር የቤት ዉስጥ ዕቃዉ አይደለም።የሥልጣን ምንጭም ሆነ ባለቤት ህዝብ ነዉ። በእርግጥ አንድ በህዝብ ተመርጦ የህዝብን አደራ መሸከም ያልቻለ ወይም በሌላ ምክንያት ሐላፊነቱን መወጣት ያቃተዉ መሪ የሥልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ቢያቀርብ ያምርበታል፤ እንደ መለስ ዜናዊ አይነቱ ህዝብን እየገደለና እያሰረ በግፍ የሚገዛ መሪ ግን ሥልጣን በቃኝ ቢል ማን ይሰማዋል? ማንስ ያምነዋል? ደግሞስ ማን የሰጠዉን ሥልጣን ነዉ በቃኝ የሚለዉ? ከፋሽስት ወታደራዊ አገዛዝ ተገላግሎ ብዙም ሳይቆይ የጠባብ ብሔረተኞች ሰለባ የሆነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ መስማት የሚፈልገዉ አንድ ነገር ቢኖር መቼ ከወያኔ እርግጫ ተገላግሎ እንደ ሰዉ መኖር እንደሚጀምር ነዉ እንጂ የመለስ ዜናዊን ማለቂያ የሌለዉ ተረት አይደለም።

ሥልጣን መልቀቅን በተመለከተ እኤአ ማርች 31 1968 ዓም እዉቁ የአሜሪካ ፕረዚዳንት ሊንደን ጆንሰን እንዲህ ሲሉ ነበር የአለምን ህዝብ ያስደነቁት፡ “ልጆቻችን ከአገራቸዉ ርቀዉ ዉጊያ ላይ ነዉ ያሉት፤እዚህ አገር ዉስጥ ደግሞ የአገራችን የአሜሪከ የወደፊት ዕጣ ጥያቄ ዉስጥ ገብቷል።እኛም ሆንን የተቀረዉ የአለም ህዝብ ለሠላም ያለዉ ትሰፋ በእንጥልጥል ላይ ነዉ፤ ከአሁን በኋላ ምንም ያክል ቢሆን ያለኝን ግዜ የማጠፋዉ የአሜሪካንን ህዝብ ተስፋ ብሩህ ለማድረግ እንጂ ለፓርቲ አሠራር ዉጣ ዉረድና ለግል ዝና አይደለም። ይህም ሁሉ ሆኖ ግን በሚቀጥለዉ ምርጫ አልወዳደርም ፓርቲዉ የሚያቀርብልኝን የእጩነት ጥያቄም አልቀበልም”

እንግዲህ ፕረዚዳንት ጆንሰን ይህንን የማያሻማ ንግግር ያደረጉት የአሜሪካ ህዝብ በድጋሚ ይመርጣቸዋል ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ ነዉ። ፕረዚዳንት ጆንሰንን ህዝብ ይወዳቸዋል እሳቸዉም ህዝብን ይወዳሉ፡ስለሆነም የወደፊት ዕቅዳቸዉን ለዚህ ለሚወዳቸዉ ህዝብ ማሳወቃቸዉ ፕረዚዳንቱ ምን ያክል ህዝብን እንደሚወዱና እንደሚያከብሩ ያሳያል።መለስ ዜናዊ ግን የህዝብን ዉሳኔ የማይቀበልና ህዝብ ጠልቶት ማን በገላገለኝ የሚለዉ ጨካኝ ሰዉ ነዉ፤ይህ አንደበቱ በክህደት ልቡ በበቀል የተሞላ ወንጀለኛ ሰዉ ኢትዮጵያን ለሌላ ተረኛ ዘራፊ አሳልፎ ለመስጠት ፈልጎ ካልሆነ በቀር ሥልጣን በቃኝ የሚልበት ሌላ ምክንያት የሚኖር አይመስለንም። አገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ ያሉ የመለስ ዜናዊ አጨብጫቢዎችም ቢሆኑ አይናቸዉ የሚያየዉን ሐቅ ልባቸዉ ማመን እያቃታዉ ነዉ እንጂ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያን የሚጠላ ከሀዲ ሰዉ ባይሆን ኖሮ የብዙ አፍሪካ አገሮችን ድንበር በሜትር ለክታ ያስከለለችዉ አገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ የራስዋ ዳር ድንበር ዬት መሆኑ አይጠፋትም ነበር።

መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ አንድ በግልጽ ሊያዉቁት የሚገባ ነገር አለ፤ ወደ ጨለማ ቤት ዉስጥ የሚገባ ሰዉ ብርሀን እንጂ ጨለማ ታቅፎ አይገባም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ያደረ ቂምና የቆየ ቅሬታ ያለበት ህብረተሰብጋ የሚሄድ ሰዉ ፍቅርና ዕርቅ እንጂ ጥላቻ ተላብሶ አይሄድም። የኢትዮጵያ ህዝብ በብርሀን ዉስጥ መኖርን እየተመኘ የጨለማ ዉስጥ መንገደኛ ሆኗል፤በፍቅር ተቃቅፎ መኖር እየፈለገ የወያኔ የጥላቻ ፖለቲካ ሰለባ ሆኗል። የፖለቲካ ድርጅቶች ድርሻ በጨዋነት መወዳደር ሲሆን የህዝብ ድርሻ ደግሞ የሚወክለዉን ግለሰብ ወይም ፓርቲ መምረጥ ነዉ፤ ወያኔና መለስ ዜናዊ ግን አንዱ መራጭ ሌላዉ ተመራጭ በመሆን ገና ከአንድ አመት በኋላ የሚደረገዉን ምርጫ ዉጤት ከአሁኑ እየነገሩን ነዉ።እነዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አሪዮስ የሚጠላቸዉ እብሪተኞች የሚቀጥለዉን ምርጫ ዉጤት በእርግጠኝነት ለመናገር መድፈራቸዉ ምን ያህል ለሌብነት መዘጋጀታቸዉን ያሳያል። የሚገርመዉ መለስ ዜናዊ በምእራቡ አለም የሚኖር የፖለቲካ ሰዉ ቢሆን ኖሮ እንኳን ህዝብ መርጦት አገር ሊመራ የራሱም ፓርቲ በእጩ ተወዳዳሪነት አያቀርበዉም ነበር።

ሌላዉ እጅግ በጣም አስቂኝ ከሆኑ የሰሞኑ ክስተቶች አንዱ መለስ ዜናዊ ካላባበላችሁኝ ሥልጣን ሊበቃኝ ነዉ ብሎ ባላዘነበት ማግስት “መለስ ሺ አመት ይንገስ” እያሉ በኩዳዴ ህዝብን የሚያዘናጉ የፖለቲካ ደብተራዎች መከሰታቸዉ ነዉ። የሚያሳዝነዉ እነዚህ “ሺ አመት ንገስ” ባዮች ሌላ ሰዉ ሳይሆን መለስ ዜናዊ እራሱ ለምን ሺ አመት ልንገስ ብሎ ቢጠይቃቸዉ እነሱ መናገር እንጂ ማሰብ፤ መብላት እንጂ መስራት የማያዉቁ ሞልቃቆች ናቸዉና መልስ የላቸዉም። እነዚህ መለስ ዜናዊን ከራሱ ጥላ በለይ ሚከተሉት ሥጋ የለበሱ ሮቦቶች ጉዳያቸዉ ከእንጀራ አባታቸዉ ከመለስ ዜናዊ ጋር እንጂ ከእናት አገራቸዉ ከኢትዮጵያ ጋር አይደለም፤ምኞታቸዉም ቢሆን የማይጠረቃዉን ሆዳቸዉን ለመሙላት ጎንበስ ቀና ማለት እንጂ ለህዝብ መቆም አይደለም። በዉል ለተረዳቸዉ ሁሉ እነዚህ የጭንቅ አዋጅ ተናጋሪዎች ቀንጨብ አድርገዉ ካሁኑ የሚነግሩን ከአንድ አመት በኋላ መለስ ዜናዊ በዋና ተዋናይነት የሚሳተፍበትን “ምርጫ” የሚባለዉን የወያኔ ድራማ ነዉ። መቼም ድራማ ሲባል አንዳንዴ ቀልድ የግድ ነዉና- እስኪ የሰሞኑን የአዲስ አበባ ቀልድ ጀባ እንበላችሁ፡ የጄኔራል አልበሺር ለፍርድ መፈለግ ያስበረገገዉ መልስ ዜናዊ አለወትሮዉ የበረሐ ቢለዋዉን ይዞ ብቻዉን ሲያወራ ጓደኞቹ ስብሐት ነጋና ስዩም መስፍን አግኝተዉት ምነዉ እንደ እብድ ብቻህን ያስለፈልፍሀል ይሉታል። አጅሬም ከተቀመጠበት ተነስቶ - አዲስ አበባ ዉስጥ አንድ ሁሉን ነገር አዉቃለሁ የሚል ሰዉ ገብቷል ሲባል ስለሰማሁ እሱን ልገድለዉ ነዉ ይላቸዋል፤ በሁኔታዉ የተደናገጡ ጓደኞቹም ትኩር ብለዉ ያዩትና በህገመንግስታችን መሰረትኮ እራስን መግደል ክልክል ነዉ ብለዉ ቢለዋዉን ያስጥሉታል።

ለመሆኑ መለስ ዜናዊ ዋሽንግተን ትዝ ሲለዉ “ፕረዚዳንት መለስ” እየተባለ ለንደን ሲታየዉ ደግሞ ጠ/ሚኒስተር ሆኖ ለ18 አመት የሙጥኝ ብሎ የያዘዉ ሥልጣን በእርግጥ በቅቶት ነዉ የሰሞኑን የሞኝ ተረት የሚተርተዉ ወይስ እንደለመደዉ የሚቀጥለዉን ምርጫ ካለ ተወዳዳሪ አሸንፎ “ህዝብ ስለፈለገኝ ነዉ እንጂ እኔስ በቅቶኝ ነበር” ብሎ ሊያሾፍ ነዉ? ደግሞስ ህወአትን ከመሰለ የወንጀለኞች መንጋ አገርን የሚገነባ አስተዋይ መሪ እንጂ መለስን የመሰለ አገር ሻጭማ መች ጠፍቶ ያዉቃልና ነዉ ከመለስ ዉጭ ሌላ አገር መምራት የሚችል ሰዉ የለም ተብሎ የሚነገረዉ ! በፊዉዳሉ ሥርአት ወቅት አፄ ኃይለ ሥላሤ ከሞቱ ኢትዮጵያ ትጠፋለች እየተባለ ይነገር ነበር፤ ዛሬ አፄ ኃይለ ሥላሤ ከሞቱ 33 አመታት ተቆጥረዋል ኢትዮጵያ ግን አልጠፋችም። የዛሬዎቹ ጎጠኞች ደግሞ የኢትዮጵያን አንድነት እንደ 17 አመት ቁምጣቸዉ በመርፌ ጠቃቅመዉ ያቆሙት ይመስል “ኢህአዴግ” ባይኖር ኢትዮጵያ ትበታተናለች ይሉናል። ይብላኝ ለኢትዮጵያዊዉ ታሪክ ፀሐፊ እየቀፈፈዉ ለሚጽፈዉ ይብላኝ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጩኸቱን ለተቀማዉ እንጂ የኢትዮጵያ ዳር ድናበር በራሷ መሪዎች ሲናድና ሲቦረቦር የታየዉ በኢህአዴግ ዘመን ብቻ ነዉ።

ወያኔም ሆነ መለስ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰላምና ብልፅግና የሚመኙ ከሆነ ያላቸዉ አማራጭ አንድ ብቻ ነዉ እሱም ከህዝብ የቀሙትን ሥልጣን ለህዝብ አስረክበዉ ወደ መጡበት መመለስ ነዉ። የቀድሞዋ ግሪክ ዉስጥ ብዙ ባሪያዎች የነበሩት ኃብታም ታላቁን ፈላስፋ አርስቶትልን ባሪያዎቼ አሳበዱኝ መኖር አልቻልኩም ምን ይሻለኛል ብሎ ጠየቀዉ፤ አርስቶትልም ጥቂት አሰበና ነፃ አዉጣቸዉ አንተም እነሱም በሠላም ትኖራላችሁ አለዉ ይባላል። እንግዲህ ከምሳሌ በላይ ማስተማሪያ ከፈላስፋም በላይ አስተማሪ የለምና መለስ ዜናዊ ከዚህ ብዙ ሊማር ይገባዋል። በዚህ ሰሞኑን በጀመረዉ አሰልቺ አንጃ ግራንጃ የህዝብን ጆሮ ከሚያደነቁር ህዝብ የጠላዉ እሱንም ፓርቲዉንም ነዉና እዉነትም ይህ ሆን ብሎ የጀመረዉ የአገር ማጥፋት ዘመቻ ሰልችቶት ከሆነ ጨርቁን ማቁን ማለቱን ትቶ በሚቀጥለዉ ምርጫ የኢህአዴግን ዉሳኔ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ዉሳኔ ለማክበር መዘጋጀት አለበት። ከሚቀጥለዉ ምርጫ በኋላ ኢትዮጵያን የሚመራዉን ሰዉ የሚመርጠዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ነዉ እንጂ ኢህአዴግ አይደለም።በእርግጥ ኢትዮጵያ ዉስጥ የአገሪቱን ርዕሰ ብሔርም ሆነ ጠ/ሚኒስትሩን ህዝብ በቀጥታ አይመርጥም፤ እንደዚህ ማለት ግን ጠ/ሚኒስትሩና ገዥዉ ፓርቲ እከከኝ ልከክልህ እየተባባሉ ከህዝብ ዉሳኔ ዉጭ ሥልጣን ላይ ይንጠለጠላሉ ማለት አይደለም።

በሚቀጥለዉ ምርጫ የኢህአዴግ ተግባር እንደማንኛዉም ኢትዮጵያ ዉስጥ እንደሚገኝ ፓርቲ ህዝብን ምረጡኝ ብሎ መማፀን ነዉ እንጂ እንደ መርዶ ነጋሪ በየመንደሩ እየዞረ ካልመረጣችሁኝ ብሎ መራጩን ህዝብ ማፈን፤ማሰር፤መግደልና ከአገሩ እንዲሰደድ ማድርግ አይደለም።ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ እንደማይወጣ ሁሉ የፓርቲና የመንግስት ኮፊያ ያጠለቁት እነ መለስ ዜናዊ ስብሐት ነጋና እነዚህ ሁለት ግላሰቦች በአምሳያቸዉ የፈጠሩት የሸክላ እቃዉ በረከት ስምኦን በአንድ ወቅት መንግስት ወይም ፓርቲ እንጂ ሁለቱንም መሆን አይችሉም።የመንግስት ተግባር በምርጫ የሚሳተፉ ፓርቲዎችንና ግለሰቦችን ደህንነት መጠበቅና የህዝብ ድምፅ በአግባቡ መቆጠሩን ማረጋገጥ ነዉ እንጂ የህዝብን ድምፅ እየሰረቀ ገዥዉን ፓርቲ በየአምስት አመቱ ሥልጣን ላይ ማስቀመጥ አይደለም። መለስ ዜናዊ እነዚህን መሰረታዊ ነገሮች ተግባራዊ ካደረገ የሚቀጥለዉ ምርጫ ብዙ ሊያሳስበዉ አይገባም እንዳዉም እሱ በትዕቢትና በማን አለብኝነት የጠየቀዉን ጥያቄ የኢትዮጵያ ህዝብ በፍቅርና በጨዋነት ይመልስለታል።

## ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ...... (ከገጽ 1 የዞረ)

ለምን ወደ ዝዋይ ማረሚያ ቤት መውሰድ አስፈለጋቸው ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የማረሚያ ቤቱ ፖሊሶች እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ። ወ/ሪት ብርቱካን ቅስሟ እንዲሰበር፣ ተረስታ እንድትቀር እንጂ ሁሌ ስሟ እንዲነሳ አይፈለግም። አሁን ደግሞ ሰው ቅዳሜና እሁድ ለጥየቃ ሄጂ ተከለከልኩ በሚል የመገናኛ ብዙሃን ሽፋን አግኝተዋል ይህ ደግሞ ከእነርሱ ፍላጎት ውጭ ነው። ስለዚህ ምን ማደረግ እንዳለባቸው ውይይት አድርገው ወደ ዝዋይ መውሰድ መፍትሄ ይሆናል ብለው ወስነዋል። ሄዶም የሚጠይቃት አይኖርም። ልጠይቃት ሄጂ ተከለከልኩ የሚልም አይኖርም። በዚያውም የእርሷንም ቅስም መስበር፣ ማሰቃየት፣ ማማረርና ተረስታ እንድትቀር ማድረግ ይቻላል። እንዲያውም የዝዋይ እስር ቤት ወባ ያለበት አካባቢ በመሆኑና በርካታ እስረኞችም በወባ ህይወታቸው በየአመቱ ለህልፈት ስለሚጋለጥ እርሷም በወባ በሽታ እንድትሰቃይ ካልሆነም ህይወቷ በወባ አልፎ መገላገል ብለው አስበው ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬያቸውን በምሬት ይገልጻሉ። ሆኖም ይህ ዜና እስከተጠናከረበት ጊዜ ወ/ሪት ብርቱካን ወደ ዝዋይ እንዳልተዛወሩ ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት...2001 ዓ.ም ቁጥራቸው ወደ ሰላሳ የሚገመቱ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ አባላት የሆኑ ወጣቶች ወ/ሪት ብርቱካንን ሊጠይቋቸው ሄደው ዛሬ ሳይሆን ሰኞ መጥታችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ እንደተባሉና እነርሱም በተባሉበት ቀን ሲሄዱ ደግሞ እስረኞች የሚጠየቁት ቅዳሜና እሁድ ነው ብሎ አበበ ዘሚካኤል እንዳላገጠባቸው ለማወቅ ተችሏል።

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ሚስት አዘብ መስፍን የኤፈር (ከገጽ 1 የዞረ)

በኢንዶውመንት ለትግራይ ህዝብ እንደተቋቋመ የሚነገርለት ኤፈረት በስሩ 25 ኩባንያዎችን እንዳቀፈ ይታወቃል። በአስራ አራት አመት ታሪኩ አንድም ጊዜ ኦትርፎ የማያውቀው እና ካለምንም ማስያዣ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ብር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚበደረው ኤፈርትን በሚመለከት የወያኔ ባለስልጣናት ጥያቄ ሲጠየቁ አይናቸው ደም እንደሚለብስ የታወቀ ነው።

ኤፈርት እራሱን የሚችል ድርጅት አይደለም፤ የኤፈርት ገንዘብ ለህዝብ ጥቅም መዋል አለበት፤ የኢትዮጵያን ህዝብ ከየባንኮቹ እየተበደረ ማክሰር የለበትም የሚሉ ጥያቄዎች ሲጠየቁ አምባገነኑ መለስ <<ይህን የሚጠይቁት የትግራይ ህዝብ ደመኛ ጠላቶች ናቸው>> እንደሚል ይታወቃል።

ኤፈረት እንደሚባለው ኢንዶዎመንት ከሆነ መሪዎችን መምረጥ ያለባቸው ዜጎች ናቸው፤ ድርጅቱም ተጠሪነቱ ለእነሱ ነው፤ገለልተኛ የሆነ ኦዲተርም በየአመቱ እየመጣ ሪፓርቱን ለህዝቡ ሊያቀርብ ይገባ ነበር ያሉት ታዛቢዎች፣ ኤፈረት ወያኔ እንዳሻው የሚዘውረው በመሆኑ ከነዚህ አንዱም እንደማይደረግ ገልጸዋል።

ተፎካካሪ ድርጅቶችን በፓለቲካ ጡንቻ እየዘረሩ የሚያስወጡት በኤፍርት ስር ያሉ ድርጅቶች ከማንኛውም መንግስት መስሪያ ቤት የተለየ እንክብካቤና ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ከማንም የተሰወረ አይደለም።

በጥረታቸው ለፍተው እና ደክመው ሀገር በሚጠቅም ስራ በተሰማሩ ባለሀብቶች ላይ ዘመቻ በመፍጠር የሚታወቀው ኤፈርት፣ መስፍን ኢንድስትሪያል የተባለውን ድርጅት ብቻ ተጠቃሚ ለማድረግ ሲባል ማሩ ብረታ ብረትን ደቁሶ ማዳከሙ ይታወቃል። የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ምርት በተጠቃሚው ተወዳጅ ቢሆንም ንብረትነቱ ኤፈርት የሆነውን የአልመዳይ ሲሚንቶን ለመሸጥ ሲባል በሙገር ምርት ላይ የተሰራው አሻጥርና ደባ በሰፊው ይታወቃል።

አዜብ መስፍን ከአባዲ ዜሙ ቀጥሎ ከፍተኛው የኤፈርት ሹም ሆና መሾሟ መለስ ዜናዊ በሚስቱ ስም ምን ያህል ዘረፋ ለማካሄድ እንደወሰነና ከትግራይ ህዝብ አብራክ በወጣው የህወሓት ታጋይና ለሆዳቸው ባደሩ ጥቂት ሹማምንት የሚዘወሩ ከብሄር ብሄረሰብ መጡ በሚባልላቸው መለዮ ለባሾች የደምና የህይወት መስዋዕትነት የገንዘብ ጥማታቸውን ለማርካት እንደወሰኑ የሚያሳይ እንደሆነ አያጠያይቅም ተብሎአል። በቅርቡ ይፋ በወጣው ዘገባ ደግሞ ከኢትዮጵያ እየተዘረፈ ወደ ሎንደን የሚመጣው ገንዝብ ባለፈው አመት በ46 በመቶ መጨመሩን ማጋለጡን መዘገባችን ይታወሳል። ህወሓት ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ያለምንም የውስጥ ተቀናቃኝ ያሻውን ለማድረግ እድል ያገኘው መለስ ዜናዊ አንኳን የሚስቱን መሾም ደፍሮ የሚቃወም ይቅርና በጥፊ ቢመታቸው የሚከላከሉ እንደሌሉበት ከታወቀ ሰንብቶአል። ከህወሓት ወጣ ሲባል ደግሞ እንደ በረከት ስምኦን፣ ተሾመ ቶጋ፣ አባዱላ ገመዳ፣ ኩማ ደመቅሳ፣ አዲሱ ለገሰ የመሳሰሉት ታማኝ ሎሌዎች እስካሉላቸው ምን ገዶአቸው? ሲሉ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከደርግ ጋር በነበረው ጦርነት የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው እና የትግራይ የጦር አካል ጉዳተኞች ማህበር ከአንድ ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት አዲስ አበባ ስታዲየም ፊት ለፊት እንደተሰጣቸው ተዘገበ። ከአዲስ አበባ ስታዲየም ፊት ለፊት ባለው እና ከጦር ማስተናገጃ ጀርባ ያለው ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣው መሬት ለማህበሩ የተሰጠው ከአስር ፎቅ በላይ እንዲሰራበት እና ህንጻውን እንዲያከራየው እንደሆነ ታውቋል።

በከተማዋ እምብርት ላይ ለየትኛውም ማህበር ሆነ ተቋም መሬት እንደማይሰጥ የገለጹት ታዛቢዎች ያሳዘናቸው ለትግራይ የጦር አካል ጉዳተኞች ቦታ መሰጠቱ ሳይሆን በባድመ፤ በሽራሮ፤ በጾረና እና በዛል አምበሳ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ምንም ዓላማ ለሌለው ጦርነት ተልከው አላስፈላጊ መስዋዕትነት እንዲከፍሉ ለተደረጉ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን እና ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን በበርካታ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ለመርዳት አንዲት ነገር እንኳን አለመደረጉ ነው ብለዋል።

ይህም በሀገሪቱ በግልጽ የሰፈነውን ፍጹም ዘረኛ አገዛዝ አስቀያሚ ገጽታ ቁልጭ አድርጎ እንደሚያሳይ አክለዋል። ለሀገራቸው የተዋደቁ ሁሉ ግደይ፤ ቶሎሳ፤ አደፍርስ በሚል ተፈርጀው ሳይለያዩ ሊከበሩ እና ሊታወሱ ሲገባ ወያኔ ግን የእኔ የሚለውን ጎጥ መርጦ ለመጥቀም መሯሯጡ አሳፋሪ ነው ተብሎአል። የወያኔን አጸያፊ ዘረኝነት የመከላከያ ሰራዊቱ አያየውም ማለት እንደማይቻል ተገልጾ በሀገሪቱ የተዘረጋው የዘረኝነት ግምብ አንድ ቀን መፍረሱ እንደማይቀር ተጠቁሟል።

## ወያኔ በሀይማኖት መሀል ጣልቃ መግባቱን አምኖ ጥፋቱን በአባላቱ አመካኘ

ወያኔ፥ ልሳኑ በሆነው አዲስ ራዕይ መጽሄት በየካቲት እትሙ አንዳንድ የራሱ መንግሥት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሃይማኖት ግጭትን በማባባስ ረገድ ሚና እንደነበራቸው ይፋ አደረገ፡፡

“ሃይማኖትን እንደሽፋን የከሠሩ ፖለቲከኞች የወቅቱ ስልት” በሚል ርዕስ በወጣው ፅሁፍ ላይ እንደተመለከተው “ከሃይማኖት ተፅእኖ ነፃ መሆን ያለበትን መንግሥት የሃይማኖት መሳሪያ ለማድረግ በሚካሄደው ጥረት ሠለባ የሆኑ የመንግሥት አካላት መኖር ነው፡፡ አልፎ አልፎ እንደሚታየው በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ አንዳንድ የመንግሥት ኃላፊነች በግላዊ እምነታቸውና በመንግሥት ኃላፊነታቸው መካከል ልዩነት ማድረግ ሲሳናቸው ይታያል” ይላል፡፡

ጽሁፉ “ሃይማኖት መንግሥታዊ አገልግሎትን ለዜጐችና ለሕዝብ ለመስጠት መስፈርት ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ በሕግ የተከለከለና የማይገባ ነው” የሚለው ልሣኑ ይሁን እንጂ ቀላል ባልሆነ ደረጃ ሃይማኖታዊ አምልኳቸው በመንግሥታዊ አገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ ጣልቃ የሚገባባቸው የመንግሥት ሠራተኞችና ኃላፊዎች እየተበራከቱ እንደመጡ ያስረዳል፡፡

“የኦርቶዶክስ አማኝ ከንቲባ ሲሆን ለኦርቶዶክስ መሬት እንደልብ የሚሰጥበት፤ የፕሮቴስታንት አማኝ ለፕሮቴስታንት፣ የእስልምና እምነት ተከታዩ ደግሞ ለሙስሊም ሃይማኖት መሬት ቅድሚያ የሚሰጥባቸው አካሄዶች በአንዳንድ አካባቢዎች በግልፅ የታዩበት ሁኔታ አጋጥሟል” የሚለው አዲስ ራዕይ በዕለት ተዕለት የአገልግሎት አሰጣጥም ላይ የሕዝብን ችግር ከመፍታት ይልቅ ሃይማኖታዊ ወገናዊነትን ታሳቢ ያደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚያካሂዱ የመንግሥት ኃላፊዎችና ሰራተኞች መኖራቸውን ያስረዳል።

በመንግሥት ኃላፊዎችና ሠራተኞች የሚደረገውንም ይህንን ዓይነት አሠራር “ፍትህ አልባነትን ከማስከተሉም በላይ የከሠሩ ፖለቲከኞች ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ግጭት ለመቀስቀስ የሚያደርጉትን ጥረት የሚያግዝ፣ የችግሩንም ትክክለኛ አፈታት የሚያወሳስብ ሆኖ ይገኛል” ይለዋል፡፡ እንደአንዳንድ የፖለቲካ ታዛቢዎች አባባል ወያኔ ዛሬ ደግሞ ማንን ሰለባ ማድረግ አስቦ እንደሆነ ባይታወቅም ከልምድ እንደታየው <ሰለባ> የሚሆን ሲዘጋጅ የተለመደ ዘዴያቸው እንደሆነ ጸሀይ የሞቀው ሀቅ ነው ይላሉ።

ወያኔ ዛሬ ለሚፈጥራቸው ቁጥር ስፍር ለሌላቸው ችግሮች የራሱን አባላትንም ሆነ ህዝቡን እንደ ከዚህ በፊቱ ጸረ ሰላም ሀይሎችና የውጭ ሀይሎች የፈጠሩት ነው ብሎ በፕሮፓጋንዳ ስራ ሊያሳምን በሚችልበት ብቃት ላይ ባለመሆኑ፣ ማጠፊያው ሲጥረው በገዛ አባላቱ ላይ ማላከክ ግድ ሆኖበታል። የሚገርመው ደግሞ በወያኔ ስርአት በፓርቲና በመንግስት መካከል ልዩነት ያለ ለማስመሰልና ፓርቲው የመንግስት ባለስልጣናትን አጋላጭ ሆኖ መቅረቡ ነው። አሁን ማን ያምነናል ብለው ነው በወያኔ ዘመን መንግስትና ፓርቲ ልዩ ናቸው ብለው የሚሰብኩን? ህዝቡ የሚለው ፓርቲውም መለስ መንግስት ማለትም መለስ ራሱ ነው፤ ኩማም ሆነ አሊ አብዶ የሚሰሩት እውነት በራሳቸው አእምሮ ነው እያሉ እያስጎመገዙን መሆን አለበት፤ ሲሉ አንድ ታዛቢ በግርምት ተናግረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ ለውጥ አድርጓል።**

በዚሁ መሰረት ከአሁን ቦኋላ **በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ** እና **በ15350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።